የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

**በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ**

ከታህሳስ 12 እስከ 17፤2017 ዓ.ም
DEC 21-27, 2024 G.C

**1.«ኢትዮጵያ በዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ከአፍሪካ አራት አገሮች ተርታ እንድትመደብ አስችሏታል» የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**

**Reporter: December 25, 2024**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት ሥነ ምኅዳር እንቅስቃሴ፣ ኢትዮጵያ በአገልግሎት ዘርፉ ከአፍሪካ በቀዳሚነት ተርታ ከተሠለፉት አራት አገሮች መካከል እንድትመደብ እንዳስቻላትና በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከ198 ሚሊዮን በላይ የዲጂታል የባንክ ሒሳቦች መኖራቸውን ቢያስታውቅም፣ የአገር ውስጥ ባንኮች ኋላቀር የመረጃ ቋት ሲስተም (Data System) ከውጭ ከሚገቡ ባንኮች ጋር የሚኖራቸውን ውድድር አስቸጋሪ እንደሚሆን ደግሞ ኤመራልድ ኢንተርናሽናል ኮሌጅ አደረኩት ባለው ጥናት መረጋገጡን ገልጿል። ቅዳሜ ታኅሳስ 12 ቀን 2017 ዓ.ም. ቡና ባንክ ከአንድ የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት አቅራቢ ጋር በጋራ በመሆን ባዘጋጀው መድረክ ላይ የተገኙት፣ የብሔራዊ ባንክ የክፍያና ሴትልመንት ሲስተምስ (Settlement Systems) ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ዳምጠው ባለፉት ስድስት ዓመታት ውስጥ በዲጅታል የፋይናንስ ዘርፉ ላይ የታዩ ለውጦችን በተመለከተ ገለጻ አድርገዋል።

https://www.ethiopianreporter.com/136725/

**2.ከሜትር ታክሲዎች የሚሰበሰበው ቫት በመያዣነት ከሚያስቀምጡት ገንዘብ ተቀንሶ ገቢ እንዲደረግ ተወሰነ**

በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ከሚቀርብ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰበሰበው የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት)፣ የሜትር ታክሲ ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች፣ ከተሽከርካሪዎች ባለቤቶች በመያዣነት ከሚቀበሉት ገንዘብ ላይ ቀንሰው እንዲያስቀሩ ተወሰነ፡፡ የገቢዎች ሚኒስቴር ለሜትር ታክሲ አገልግሎት ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች በላከው ደብዳቤ ላይ እንደገለጸው፣ በየዕለቱ መጨረሻ ለትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እንዲሰጡ አሳስቧል፡፡ ከሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ አዲሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በሥራ ላይ መዋሉ የሚታወስ ሲሆን፣ በአዋጁም አሽከርካሪውን ጨምሮ ከስምንት ሰው በታች የመጫን አቅም ያለው ተሽከርካሪ በመጠቀም የሚሰጥ የትራንስፖርት አገልግሎት የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) እንደሚከፈልበት ተደንግጓል፡፡ የገቢዎች ሚኒስቴር እንዳስታወቀው አዋጁ በደነገገው መሠረት ታክሱን ለመሰብሰብ ደንብ፣ መመርያ፣ እንዲሁም የአሠራር ሥርዓት ያልተዘረጋለት በመሆኑ ከሥራ ዘርፉ ባህሪ አኳያ ታክሱ በማን አማካይነት ይሰብሰብ የሚለው በእንጥልጥል ቆይቷል ብሏል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/136639/

**3. የኢትዮጵያን ወጪና ገቢ ንግድ የሚያሳልጥ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ግንባታ ትኩረት ተሰጥቶታል- ርዕሰ መስተዳድር አወል አርባ**

**ታኅሣሥ 17/2017**

የኢትዮጵያን የወጪና ገቢ ንግድ ማሳለጥ የሚያስችል የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አቅምን የማሳደግ ሥራ ትኩረት እንደተሰጠው የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር አወል አርባ ገለጹ።

ርዕሰ መስተዳድሩ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት የለውጥ ዓመታት የገቢና ወጪ ንግድን ጨምሮ ፈጣን ሁሉን አቀፍ ዕድገት እያስመዘገበ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያን ታላቅነት የሚመጥን የኢኮኖሚ ግንባታ የሚሳካው ለምርቶች ዝውውርና የገበያ ሰንሰለት ብቁ የማጓጓዣ ስርዓት በመፍጠር ነው ብለዋል።

ሎጂስቲክስ የኢኮኖሚ የደም ስር ነው ያሉት አቶ አወል፤ መንግሥት እያደገ የመጣውን የገቢና ወጪ ንግድ የሚያሳልጥ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አቅም በመገንባት ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

ፈጣንና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሎጂስቲክስ አገልግሎትን ዕውን ለማድረግ ለዘርፉ መሰረተ-ልማት ግንባታ ትኩረት እንደተሰጠው ገልጸዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5696078

**4. በፈተና ውስጥ አበረታች ለውጥ ያሳየው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ**

**December 26, 2024**

የአንድ ሀገር እድገት የሚለካው ኢንዱስትሪው ባለበት የእድገት ደረጃና ለኢንዱስትሪ ባለው ምቹ ሁኔታ ስለመሆኑ ይገለጻል። አንዳንድ ሀገሮች ያደጉ ሀገራት ተብለው የተለዩት በኢንዱስትሪው ዘርፍ ልቀው በመገኘታቸውና ከራሳቸውም አልፈው የዓለምን ገበያ መቆጣጠር በመቻላቸው ነው።

ኢትዮጵያ የዚህን የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ሚና በሚገባ ተገንዝባ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥታ መሥራት ከጀመረች ቆይታለች፡፡ ይህ ትኩረቷ ኢኮኖሚዋን ከግብር መር ወደ ኢንዱስትሪ እስከ ማሸጋገር ያዘለቀ ነው፡፡ ሀገሪቱ ይህን ያህል ትኩረት ሰጥታ መሥራት ውስጥ ስትገባም ብዙ ነገሮችን ታሳቢ አድርጋለች፡፡ ከእነዚህም መካከል ለዘርፉ ምቹ ሁኔታ ካላቸው ሀገሮች አንዷ መሆኗ ይጠቀሳል፡፡ የሰው ኃይል፣ ጥሬ እቃ፣ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ለባሕር በር ያላት ቅርበትና ሀገሪቱ በዘርፉ ለሚሰማሩ የፈጠረቻቸው የሕግና የመሳሰሉት ማሕቀፎች በኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ባለሀብቶችና ሀገሮች ምቹ እንድትሆን የሚያደርጉ ናቸው።

ምቹ ሁኔታዎቹን ተከትሎ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ በስፋት እየተሠማሩ ይገኛሉ፡፡ ሀገሪቱ የውጭ ባለሀብቶች ይዘዋቸው የሚመጡት ቴክኖሎጂ፣ እውቀትና ካፒታል ይዘው ለሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለውን ከፍተኛ ፋይዳ ታሳቢ በማድረግ ለባለሀብቶቹ ምቹ ሁኔታ መፍጠሯን አጠናክራ ቀጥላለች፡፡ ይህን ተከትሎም በዘርፉ የሚሰማራው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እየጨመረ ይገኛል፡፡

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩም እንዲሁ በየጊዜው የተለያዩ ማበረታቻዎችን ስታደርግ ቆይታለች፤ ለውጭ ባለሀብቶች ብቻ ክፍት ተደርገው የኖሩትን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም ክፍት አድርጋለች፡፡ ይህን ተከትሎም ባለሀብቶቹ ወደ ፓርኮቹ እየገቡ ናቸው፡፡

https://press.et/?p=143813

**5. Ethiopia requires USD 300 bln to fill climate finance gap by 2030**

**The Reporter: December 21, 2024**

The Ministry of Finance says Ethiopia will require up to USD 300 billion in climate financing by 2030.

The substantial funding will go towards the government's ambitious target to reduce emissions by close to 70 percent within five years, which was set out in the country's first updated Nationally Determined Contributions (NDCs) in 2020.

The government is working to submit updated NDCs in the coming year, which will reportedly feature details on a Climate Resilient Green Economy strategy (CRGE), Ethiopia's 10-Year Development Plan, the Green Legacy Initiative, and the National REDD+ Strategy, among others.

The CRGE strategy was first put forward during COP17 in Durban, South Africa, in 2011.

https://www.thereporterethiopia.com/43018/#google_vignette

**6.Ethiopian, China Agricultural Institutions Seeking Collaboration in Crop & Animal Production**

**ENA: December 27/2024**

The agricultural institutions of Ethiopia and China have been seeking collaboration in spheres of crop and animal production.

Ethiopian Ambassador to China, Tefera Derbew held talks with leaders from the Ethiopian Institute of Agricultural Research (EIAR) and the Beijing Academy of Agriculture and Forestry Sciences at the Embassy today.

The discussions emphasized the importance of enhancing cooperation between the two organizations, according to the Embassy of Ethiopia in Beijing, China.

Accordingly, both institutions have agreed to sign a Memorandum of Understanding (MoU) in the areas of crop and livestock production.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5700633

**8. Ethiopia's Production Capacity of Manufacturing Industries Jumps to 60 Percent**

**ENA: December 26, 2024**

The production capacity of Ethiopia's manufacturing industries has risen to 60 percent, according to Ministry of Industry.

Industry Minister and Prosperity Party Executive Committee member, Melaku Alebel, said that the growth was achieved by addressing the challenges faced by the sector.

Recall that a new policy has been implemented in recent years to enhance the contribution of manufacturing to the economy and address gaps.

The policy aims to leverage the potential of the sector and capitalize on emerging opportunities while adapting to the evolving dynamics of the industry.

The minister also emphasized the significant progress made in overcoming the challenges within the sector, which has enabled it to become more competitive.

Melaku credited the 'Made in Ethiopia' movement, launched two years ago, for playing a key role in improving competitiveness by tackling critical issues in the sector.

The government has designed and implemented policies that support both domestic and export production.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5697551

**9. GIZ, Private Sector and Gov't Partnership Successful: Country Program Head Waldamann**

***ENA: December 25/2024***

The partnership between GIZ Ethiopia, the Ethiopian Government and the private sector is bearing fruit in various areas, according to GIZ Ethiopia Program Head Anna Waldamann.

The program head told ENA that the partnerships of GIZ with Ethiopian Government institutions and the private sector is cooperative, constructive and successful.

She said GIZ is working on different levels to promote private sector development.

For instance, it has been working with the government to provide policy advisory in the field of creating a better business environment, the head added.

"We also work with business associations to help them strengthen and deliver better services for their members, and advocate for the policy changes they want to see. Besides we work with companies directly to increase their production capacity so that they can produce more, sell more, and create more jobs."

In general, "I would say our partnership and cooperation is constructive," Waldamann underscored.

According to her, the corporative and constructive partnership of GIZ is demonstrated by support and engagements with government institutions and the private sector.

She mentioned as an example the support GIZ extended to the Public-Private Dialogue (PPD) on the economic reforms organized by Ministry of Industry last week.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5691331